# የአዲስ አበባው መአከላዊ እሥር ቤት ቤተመዘክርና ሮቢን ደሴት/Robben Island/ ቤተመዘክር ሲነጻጸር

ወልዳአብ ደንቡ

ሐሙስ ጥር 24/ 2010
(Feb 01/02/18)

ለማኅበራዊ ፍትኅ፣ለኅገ የበላይነት፣ለመልካም አስተዳደር ወዘተርፈ ጠበቆችን በማሰቃየት ፍጹም አምባገነናዊ የፖለቲካ ሥርዓት ማስፈጸሚያና ማስረዘሚያ በሆነው በማዕከላዊ እሥር ቤት የሚገኙትን እሥረኞችን ፈትተው ወደ ቤተመዘክርነት እንደሚቀየር በህወሃት ተላላኪ በአቶ ሃይለማርያም ደሳለኝ ሲገለጽ -ኢትዮጵያውያንን አስደስቷል፣አስፈንጭቷል። ህወሃት ለብሄራዊ እርቅ መዘጋጀቱ ይሆን? ሕዝባዊ አመጹን አስገድዶት ይሆን?ምንያህል እሥረኞች ይፈቱ ይሆን? አፈታቱስ እንዴት ይሆን ? የሚፈታው መንግሥት ማለት ሕግ ወይስ የፖለቲካ ፓርቲ ወዘተርፈ ? በተሰኙ አሻሚ አሳቦች ላይ ከአራቱ የሉል/የግሎብ ማዕዘናት ኢትዮጵያውያን አወያይቷል ፤አከራክሯል።የእስረኞች መፈታት ቶሎ እውን ባለመሆኑ ወይም በመዘግየቱ ኢትዮጵያውያን ወዠነበረ፣ግራአጋባ፣አወዛገበ። ለፖለቲካዊ ሥልት ነው፣ለአመጽ የተዘጋጅን ሕዝብ ለማዘነጋትና ጊዜ ለመግዛት ነው፣ ህወሃት የሥልጣን ዕድሜውን ለማደላደልና ለማራዘም የረዱትን ምዕራባውያን መንግሥታትን ለመሸወድ/ለማታለል ፣ ከኤርትራ ጋር ለመዋጋት ስለተዘጋጀ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጎኑ ለማሰለፍ ነው ወዘተርፈ ተባለ ። እስቲ ይህ በዚህ እንዳለ ትቼ በተነሳሁበት አርእስት መልዕክት ወደ ማስተላልፍበት ጽሁፍ ላምራ።

የሮቢን ደሴት ቤተመዘክር የአፓርታይድ ሥርዓት መሸነፍ ወይም መገርሰስ ውጤት ነው ። በደቡብ አፍሪካ እ.ኤ.አ ከ1948 -1990 ዓ.ም የቀየው፣በተለያዩ ዘረኛ መሪዮችና በዘረኛ የፖለካ ፓርቲዮች የተመራው የአፓርታይድ ሥርዓት እና እ.ኤ.አ ከ1991 ዓ.ም ጅምሮ አገራችን እየገዛ ያለው የህወሃት ሥርዓት የአንድ ሳንቲም ፊትና ኋላ ናቸው ። የሁለቱም ፖለቲካዊ፦ እርዮት፣ ጥመቃ <indoctrination>፣አወቃቀር <structure> ፣ ፖሊሲ፣ጽርጸት <discourse> ፣ መተገበርዖት <discursivelity> ወዘተ.. የዘርመድሎ መሰረት ያደረጉ ናቸው ። ሁለቱም በሥነ-ፍጥረት/በባዮሎጂ እና በዘር ምህንድስና (eugnics) የእኛ ዘር ሃያል ነው፣ ስለሆነም በባዮሎጂና በዘር ምህንድስና ዝቅተኛና ደካማ የሚልዋቸውን መግዛት የተፈጥሮ መብታችን ነው ያሉ/የሚሉ ናቸው ። ሁለቱም እነሱ ወይም እነዚያ የሚልዋቸውን የሚንቁና የሚጠሉ ናቸው ፤ሁለቱም ሌሎች በሚልዋቸውን <at the expense of> (መፈናቀል፣ ሞት፣ ድኅነት፣ጉስቁልና፣በሽተኝነት፣ ድንቁርና ወዘተርፈ) የእኛ የሚሎቸውን ያበለጽጉ ፤በሃብት ያጥለቀልቁ፣ የተለየ የትምህርት ሥርዓት የቀየሱ ፤የተለየ የጤና አገልግሎት መስጫ የቀየሱ፣ እነዚያ የሚሏቸውን አሽከርና ገረድ ያደረጉ ወዘተርፈ ናቸው ።

በደቡብ አፍሪካው አፓርታይድ ሥርዓት፣ እነዚያ ዝቅተኞች፣ ለመግዛት ሳይሆን ለመገዛት የተፈጠሩ ተብሎ የተመደቡት (ጥቁሮችና ባልቅይጥ ቀለሞች) ሲሆኑ በህወሃት የአገዛዝ ሥርዓት 80-1 =79 ብሄረሰብዎች/ነሳዎች ሁሉ ዝቅተኞችና ለመገዛት የተፈጥሩ ተብልው የተመደቡ ናቸው።ማለት የትግሬ ዝርያ ያላቸው ብቻ ፦ ለመግዛት፣ለማስተዳደር፣ለጀግንነት፣እውቀት ለመገበየት፣አስተውሎ ለመናገር ወዘተርፈ የተፈጠሩ ናቸው።ጥንታዊው የግሪክ ፈላስፋ ‵ፕሌቶ′ የግሪክ ግዛቶች <Estates> ለማስተዳደር ብቃት ያላቸው ‵ፈላስፋዎች′ ብቻ ናቸው እንዳለው ዓይነት ነው ። የአፓርታይድ ሥርዓትና የህወሃት ሥርዓት አንድነት እንዳላቸው ሁሉ ልዩነትም አላቸው ።

- ቅርጽ - የደቡብ አፍሪካው የዘር መድሎ/የአፓርታይድ ሥርዓት የተፈጸመው የነጭ ዘር በጥቁር ዘር ላይ ሲሆን፣የህወሃቱ የዘር መድሎ የተፈጸምውና እየተፈጸመ ያለው የጥቁር ዘር በጥቁር ዘር ላይ ነው ። በዚህ ምድር የተለያዩ የቆዳ ቀለም ያላቸው ሰዎች ሁሉ ዝሪያ ግኝት/ምንጭ አገራችን ኢትዮጵያ መሆኗ የመስኩ ጥናት ሊቃውንቶች/ሳይንትስቶች አረጋግጠው ይፋ ከሆነ ብዙ ዓመታት ሆኖታል፤ ለጭብጥነቱ (BORN IN AFRICA;THE QUEST FOR THE ORIGINS OF HUMAN LIFE by Martin Meredith)) ማንበብ ያስፈልጋል።ይሁን እንጂ የወያኔዎች ድንጋያማ/ጭንጫማ ጭንቅላቶች ይህንን ሃቅ መቀበል ባለመቻሉ፤አንድ የዘር ምንጭ ያላቸው፣ በቁጥር 80

የሚደርሱ ጥንታዊ <indigenous> ብሄረሰብዎች/ጎሳዎች፣ከተለያየ አገር የመጡ፣የተለያየ የዘር ዝሪያ ያላቸው አድርጎ በመሥበክና በመሸንሸን ከፋፍሎ ገዝቷል፤እየገዛም ነው።

- አገራዊ ሉዓላዊነት <Sovereignty> - የደ/አፍሪካው የአፓርታይድ ሥርዓት፣ የደቡብ አፍሪካን ሉዓላዊነትና ዳርድንበር አላስደፈረም፣አገር አላስገነጠለም፣ደቡብ አፍሪካ የባህር ሃይልና የባህር በር/በሮቹ አልባ አላስደረገም
- እድገት -የአፓርታይድ ሥርዓት ደ/አፍሪካን ከየትኞችም በኢንዱስትሪ፣በቴክኖሎጂና በምጣኔ ሃብት አደጉ ከሚባሉት ፣ ምዕራባውያንና ምሥራቃያን አገሮችን አሥበልጦ/አቻ አድርጎ አለማት እንጂ አላቀጨጫትም።
- የአፓርታይድ መሪዮች/ሚኒስትሮች በብዙ ቢሊዮን ወይም ሚሊዮን የሚቅጠር ዶላር/ራንድ ከደ/አፍሪካ እያሸሹ በባዕዳን አገሮች ባንኮች ያከማቹ ነበር ተብሎም/ተሰምቶም አይታወቅም።
- የአፓርታይድ መሪዮች የእኛ መሠረት ሆላንድ ስለሆነ የደቡብ አፍሪካ የሃብት ምንጭ ሁሉ ወደ ሆላንድ ካልሄደ/መሄድ አለበት አላሉም ።
- የደ/አፍሪካን -የታሪክ፣ የባህል፣የሳይንስ የመከላኬያ፣የትምህርት ወዘተርፈ ቅርሶች፣ ተቋሞችና የተፈጥሮ ሃብቶች አልደመሰሰም ፤ነቃቅለው ወደ ሆላንድ አልወሰዱም
- የአፓርታየድ ሥርዓት መሪዮች - ደቡብ አፍሪካ የመቶ ዓመታት ታሪክ ብቻ አላት፣ ባንድራዋ ተራ ጨርቅ ነው፣ የደቡብ አፍሪካ ሕዝቦች በምን አይገኛኙም፣ ዙሉዎች የፈጸሙትን ጀግንነት ለዙሉዎች እንጂ ለሌሎች ደ/አፍሪካ ጥቁሮች ምናቸውም አይደለም ወዘተርፈ ብለው አልሰበኩም፤አልደሰኮሩም ።
- በአፓርታይድ ሥርዓት ጥቁሮችና ባልቅይጥ ቀለሞች- የሚበሉትን ፣የሚጠጡትን እና የሚጠለሉበትን አጥተው ሲሰደዱ፣ (አውሬ፣ዘንዶ፣ባህር) ሲበልዋቸው ፣ሲታረዱ፣ሲሸጡ ወዘተርፈ አልታዩም/አልተሰማም
- የአፓርታይድ ሥርዓት የደ/አፍሪካ ጥቁሮችና ባለቅይጥ ቀለሞች ላይ ሁለገብ ጭቆና ቢፈጽምባቸውም :- የቻይና፣ የህንድ፣የአረብ አገሮች ወዘተ..ኩባኒያዎች ዘመናዊ ባሬያዎች አላስደረጋቸውም
  ባጭሩ የህወሃት/ወያኔዎች ሥርዓት ከደቡብ አፍሪካው አፓርታይድ ሥርዓት እጅግ በጣም የከፋ መሆኑን የሚያሳዩ በጣም ብዙ ማስረጃዎች ያሉ ሲሆን እነዚህ ጥቂቶቹ ናቸው ።

በማኅበራዊና በልማዳዊ እውቀት የበለጸጉ ቀደምቶቻችን "ነገር ከሥሩ ውሃ ከምንጩ" በማለት እስተምረውናል ። ስለሆነም ስለ ሮቢን ደሴት 'ቤተመዘክር' ለመጻፍ ፣"የሮቢን ደሴት/Robben Island" በጣም አጭር ፖለቲካዊ ታሪክ እስላለሁ/አስጨብጣለሁ። ሮቢን ደሴትም ሆነ ቤተመዘክሩ የሚገኙት ኬፐታወን/Cape Town ተብሎ በሚጠራ ክ/ሃገር ነው ። ሮቢን ከዋናው የኬፐ/Cape ምድር በባህር /በውሃ ተከፍሎ ድሴት ከመሆኑ በፊት ለብዙ ሺህ ዓመታት ሰዎች ኑሮውበታል። ከ1600 አጋማሽ እስከ 20ኛው ዓ/ም ማልቂያ አካባቢ በደቾች/በሆላንዳውያን ቅኝ ሥር ወደቀ ።

ሮቢን ደሴት- የፖለቲካውን ሥርዓት የማይፈለጋቸው ሰዎች(unwanted people) ማጠራቀሚያ ነበር። ምሥራቃዊና ደቡባዊው -ደቡብ አፍሪካ ቅኝ ይገዙ የነበሩትን ሆላንዳውያን ተጻሮ ይፋለሙ የነበሩትን፣እንግሊዞች በአፍሪካ ምድር ያሰፈኑትን ሰፊ ቅኝ ግዛት/ኢምፓየር የተቃወሙትን፣የእስልምና ሃይማኖት መሪዮችን፣ የጦር ምርኮኞችን፣ወንጀለኞችን፣ የቁምጥና ታማሚዮችን፣የአእምሮ ህመምተኞችና የ20ኛው መቶ ክ/ዘመን ጸረ-አፓርታይድ ታጋዮችን እየወሰዱ የሚያጉርበት እና በሁለተኛው የዓልም ጦርነት ለወታደራዊ ምሽግ/ለሚሊታሪ ቤዝ የተጠቀሙበት ሥፍራ ነው ።




አንጋፋ ጸረ-አፓርታይድ ታጋዮች እ.ኤ.አ በ1998 ማለቂያ አካባቢ፣ ማንዴላ በፌብረዋሪ 11/1990 ዓ.ም፤ሌሎች የፖለቲክ እሥረኞች የ1994 ምርጫ ከመደረጉ በፊት ከደሴቱ እስር ቤት የተፈቱ ሲሆን ፤የመጨረሻዎቹ የሕግ እሥረኞች እ.ኤ.አ ጄንዋሪ 1/1997 ዓ.ም ከደሴቱ ተለቀቁ ።

የሮቢን ደሴት ቤተመዘከር- የደቡብ አፍሪካ ልዩ ብሄራዊ ቅርስ(NATIONAL HERITAGE SITE) እና በተባበሩት መንግሥታት የዓለም የትምህርት፣የሳይንስ እና የባህል ድርጅት ቅርስ (UNESCO-WORLD HERITAGE SITE)መሆኑን እ.ኤ.አ 1999 ዓ.ም ይፋ ሆነ። ቤተመዘክሩ ከደቡብ አፍሪካ ልዩ ብሄራዊ ቅርሶች አንዱ ሆነ ፤በተባበሩት መንግሥታት የዩኔስኮ (UNESCO) ቅርሶች ውስጥ ተመዘገበ ሲባል የሚሰጠው ትርጉም ምንድነው?

**ሀ) (1) ተወልደን ያደግንበትን አገር፣ ያያት የቅድመ አያቶቻችን አገር፣ ዘር ማንዘሮቻችን የኖሩበትን ደቡብ አፍሪካ ወስዳችሁ እንደ ባዕድ ፤እንደ ንዑስ ዜጋ አትቁጠሩን፣ የዘር መድሎ አታድርጉብን ፤አትበድሉን፣ አትጨቁኑን ፤አገራችን ለቃችሁ ሂድም አላልንም ፤ የትኛውም ደቡብ አፍሪካዊ ጎሳና ግለሰብ ያላገለለ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት መሥርተን በእኩልነት ፤ በሰላም ፤ በመቻቻል፣ በፍቅር ወዘተርፈ አብረን እንኑር ብለው አቤት በማለታቸውና በመታገላቸው የደረሰባቸውን ኢሰብአዊ ፦ ግፍ፣ እንግልት፣ እስር ወዘተ..(2) በእነዚሁ ታጋዮች የሕይወት ዘመን የግፈኞችና የዘረኞች የዘረኝነት እርዮት ዓለምና ፖሊሲ ተሸንፎ ፤ የታገሉለትን መተክልና ራኢ እውን ሆኖ፣ አሮጌውን ደቡብ አፍሪካ የዘር መድሎ በሌለበት በአዲሱ ደቡብ አፍሪካ መተካት፣ የመጠቁ ንቃተ ኅሊናዎችና ዕጹብ መንፈስዎች (Enlightened Consciousness and Noble Spirits) አሸናፊና ሕያው ሆነው ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲታወሱ የሚኖሩ መሆናቸውን ለማስረገጥ።**

**ለ) ቤተመዘክሩ ጎብኞችን- የደቡብ አፍሪካውያን ሁለት ተጻራሪ ፖለቲካዊ ታሪክ (political history) ለማስተማር ። ማለት (1) አሮጌውን፣ቆሻሻውን፣ዘረኛውን ፤ከፋፋዩን ወዘተ..መንግሥታዊ ሥርዓት ምን ይመሥል እንደነበረ (2)ደቡብ አፍሪካ የሁሉንም ደቡብ አፍሪካውያን ባህል ፤ሃይማኖትና ቋንቋ በእኩልነት በስሚስተናገዱበት ፤ሰብአዊና ፖለቲካዊ መብቶች በተከበሩበት፣ፍትህና የሕግ የበላይነት በሰፈነበት ፤ በአዲሱ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዴት እንደተተካ ለማስተማር ።**

**ስለአፓርታይድ ሥርዓት መወገድ ጅምር እንዴት ነበር?** በአፓርታይድ ሥርዓት የወቁቱ የብሄራዊ ፓርቲ (National Party) መሪና በውቅቱ የደቡብ አፍሪካ ፕሬዝዳንት የነበሩት አቶ F.W.De klerk - አንጋፋ ጸረ-አፓርታይድ ታጋዮችን እ.ኤ.አ በ1998 ማለቂያ አካባቢ፣ ማንዴላ በፌብረዋሪ 11/1990 ዓ.ም ከፈቱ በኋላ በአፓታይድ ሥርዓት መወገድ ምክር ቤቱ እንዲወያይበት አደረጉ። ምክርቤቱም በአፓርታይድ ሥርዓት መወገድ ላይ እጅግ በጣም አብላጫ በሆነ ድምጽ ወሰነ። በመቀጠል አቶ F.W. De Klerk የነጭ የበላይነት በአስቸኳይ መወገድ አለበት በማለት ንግግር አደረጉ። ከዚያም የብሄራዊ እርቅ ሂደት

ተጀመረ።በዲክለርክ መንግሥት፣በገዡ ብሄራዊ ፓርቲ፣ በደቡብ አፍሪካ ብሄራዊ ምክርቤት(ANC) እና በሌልች የፖለቲካ ድርጅቶች መካከል ሦስት ዓመት የፈጅ (1990-93) የዘለቀ የደረጃ በደረጃ ውይይቶች፣ ድርድሮችና ስምምነቶች መሠረት ወደ 1994 ብሄራዊ ምርጫ ተገባ/ተገበረ።

የጠፈርም ሆነ የምድር ይሁንታዎችና ክንውኖች ሁሉ ምክንያትያቶች አሏቸው ፤ አንዳችም ነገር ያለምክንያት እንደማይሆን ግልጽ ነው፣ ታዲያ የአፓርታይድ መወገድ ምክንያቶች ምንና ምን ይሆኑ? የአፓርታይድ መወገድ ምክንያቶች በርካታ ቢሆኑም፤ የሚከተሉት አንኳሮቹ ናቸው :-

- ጸረ-አፓርታይድ :-አድማዎች፣አሻጥሮች፣ ሰላማዊ ንቅናቄዎች፣ኢሰላማዊ አመጾች እየጨመሩና እያደጉ መምጣት
- በደቡብ አፍሪካ -ኢኮኖሚ ፣ንግድ፣ስፖርት ፣ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት፣ጎብኛች/ቱሪዝም ወዘተርፈ ላይ ሙሉ/ቶታል እቀባዎች በመደረጋቸው
-በማንዴላ ይመራ የነበረው የደቡብ አፍሪካ ብሄራዊ ምክርቤት (ANC) ሆነ የመሪዮቹ ርዮዮትና ፖሊሲ ነጭዎች ከአገራችን ፣ ይውጡ ፣ይወገዱ የሚል አልነበረም። የታገሉት የዘር መድሎ/አፓርታይድ ተወግዶ፣ በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት በደቡብ አፍሪካ ምድር የሚኖር የሰው ልጅ ሁሉ በዕኩልነት ይኑር፣እንኑር በሚል ነበር። ያ ታሪክዊ ወቅት፣ ያ እጅግ በጣም የሰለጠነ አስተሳሰብ ፣ያ እድል ያለመጠቀም የኋላ የኋላ የሚያስከፍለውን አሉታዊ ዋጋ/ጠንቅ በመረዳት። ማለት "ሲለምንዋት ትታ ሲጎትቷት" እንደሚባለው ፣ሆይ ብሎ ተነስቶ ነጭ ከሃገራችን ካልውጣ በማለት ነጭን የሚጨፈጭፍ ትውልድ ሊሚጣ እንደሚችል ግምት ውስጥ በመከተት ወዘተርፈ ፤የአፓርታይድ ሥርዓት መወገድ በማንዴላ የሕይወት ዘመን መሆን እንዳለበት ስለተረዱ (for being an imperative)

**ማዕከላዊ እሥር ቤት ወደ ቤተመዘክርነት መቀየር**

የወያኔዎች መልዕክተኛው አቶ ደሳለኝ ሃ/ማርያም ማዕከላዊ እሥር ቤት ከእሥር ቤትነት ወደ ቤተመዘክርነት መቀየር ምክንያት ሲሰጡ "በደርግ ዘመን ስለማዕከላዊ ሲነሳ በርካታዎች የተሰቃዩበት ቦታ ነው" ካሉ በኋላ፣ "አገራዊ መግባባት ለመፍጠር ፣የዲሞክራሲያዊ ምኅዳር ለማስፋትና የመደብለ ፓርቲ ሥርዓት ለማስተናገድ" ጅምር እንደሆነ ጠቁሟል። መመኘት፣ማውራት፣ማሰብ .. እና ተግባር እየብቻ ናቸው ። የሰማይ ማማ ሆኖ ባይቀር ኖሮ እሰይ የሚያሰኝ ስልጡን እሳቦት ነበር።

ማዕከላዊ እሥር ቤት ወደ ቤተመዘክርነት እንለውጠዋለን ሲሉ ፤ የወያኔዎች ሥርዓት ባለበት ወይስ ከተወገደ በኋላ ማለታቸው ነው ? በዚህ ጽሁፍ ከላይ እንዳስጨበጥኩት የሮቢን ደሴት ወደ ቤተመዘክርነት የተቀየረው የአፓርታየድ ሥርዓት ተወግዶ ኔልሰን ማንዴላ የደ/አ መሪ በሆኑበት እ.ኤ.አ በ1997 ዓ.ም ነው ። ስለሆነም ማዕከላዊ እሥር ቤት ወደ ቤተመዘክርነት መቀየር የሚችለው የወያኔዎች ሥርዓት ተወግዶ፤ በኢትዮጵያ ሕዝብ አመኔታና በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የተመረጠ መንግሥት ሲመሠረት ነው።

### "በደርግ ግዜ ስለማዕከላዊ ሲነሳ በርካታዎች የተሰቃዩበት ቦታ ነው" <አቶ ሃ/ማርያም ደሳለኝ>

ይህ አባባል 'የአብዬን ወደ እምዬ' አይሆንምን? ወይም 'የራስዋን አሮባት የሰውን ታማስላለች' አይሆንምን? በዚህ እሥር ቤት ኢሰባዊ ግፍና ሰቆቃ የተፈጸመው በደርግ ሥርዓት እንጂ በወያኔ ሥርዓት አይደለም ለማለት ነውን? በወያኔ ሥርዓት በዚህ እሥር ቤት አንዳችም መጥፎ ነገር አልተሠራም ለማለት አይደለምን? ደርጎች የሠሩትን አስከፊ ድርጊቶች እኛ የመካስ ሃላፊነት አለብን አይመስልምን? 'አባት ባጠፋው ልጅ አይቀጣም' እንደሚባለው፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ወያኔዎች የሚቀጣው በወያኔዎች ጥፋቶች እንጂ በደርግ ጥፋቶች አይደለም።

ለሥልጣንና ለተደላደ ቁሳቁሳዊ/material ሕይወት ፣አውሬዎች/beasts በሚያድንዋቸው እንስሶች ላይ የማይፈጽሙትን ዓይነት ጭካኔ ፤ በዚህ በማዕከላዊ እሥር ቤት:- የፈጸሙም ያስፈጸሙም፣የረሸኑም ያስረሸኑም፣የገደሉም ያስገደሉም፣ቀይ ሽብር ያስፈጸሙም የፈጸሙም ፣ሰቆቃ/ቶርች የፈጸሙም ያስፈጸሙም ወዘተርፈ ደርጎችና ጀሌዎቻቸው በሕይወት ስላሉ እነሱ ይጠየቁበታል። እሥር ቤቱ ወደ ቤተመዘክርነት ሲቀየር ከላይ እንደጠቀስኩት ፣በደርግ ዘመን በዚህ እሥር ቤት ስቆቃ ተፈጽሞባቸው በሕይወት ያሉትን፣ሰቆቃ/ቶርች ሲፈጸምባቸው የሞቱትን፣አካለስንኩል የሆኑትን ፣በቅይ ሽብር የሞቱትን ሁሉ ስምና ምስል ለቤተመዘክሩ ማስረከብ አለባቸው። ማለት ቤተመዘክሩ በእነዚህ ሁለት ሥርዓቶች የተፈጸሙትን ሰቆቃዎች የሚዘክር/የሚያስታውስ፣ ለነገው ትውልድ መማርያና ማስተማርያ ፣የመጥፎ ታሪካችን ቅርስ ይሆናል ማለት ነው ።

ወያኔዎች - አገራዊ መግባባት ለመፍጠር፣የዲሞክራሲያዊ ምኅዳር ለማስፋት እና የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት ለማስተናገድ" ጅምር እንዲሆን እሥረኞችን ፈትተን ፣ማዕከላዊ እሥር ቤት ወደ ቤተመዘክርነት እንቀረዋለን የሚል መግለጫ ለመስጠት ያስገደዳቸው ምን ይሆን?

<ግፍ፣ጭቆና፣ድኅነት፣ረሃብ፣ባርነት> ወዘተርፈ አንገፍግፎት ከየአቅጣጫው የተነሳውን ሕዝባዊ አመጽ፣ ከምዕራባውያን መንግሥታት የሚያገኙትን የገንዘብ ድጎማ መቀነስ ፣የምዕራባውያን መንግሥታትና ለሰብአዊ መብቶች ተሟጋች ድርጅቶች ጫና፣ከሌሎች አገሮች ለመገበያየት/ሸቀጦች ወደ አገር ለማስገባትና ከአገር ለሚወጡት የውጭ ምንዛሪ እጥረት፣ የብር ዋጋ ከፉኛ መውደቅና የገበያ ዋጋ መናር፣የብሄራዊ እርቅ ውትወታ ወዘተርፈ **ግፊቶች<preasures>** ለማስተንፈስ ተጠቀሙበት እንጂ፣እነዝህን ግፊቶች አምበርክኳቸው ፤ አውነትም "አገራዊ መግባባት ...፣የዲሞክራሲያዊ ምኅዳር.. እና የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት ለማስተናገድ" አይመስለኝም፤አይደለምም **።ያ ቢሆን ኖሮ በወልዲያ፣በቆቦ፣በመርሳ፣በሳርቃ ወዘተ.. የፈጸሙትን ዓይነት ጭፍጨፋ አይፈጽሙም ነበር። ፖለቲካዊና ሰብአዊ መብቶች በተከበሩባቸው አገሮች ሰላማዊ ሰልፈኞችን የሚያስተናግዱበትና የሚቆጣጠሩበትን አይነት ሥልጡን ዘዴዎች መጠቀም ይችሉ ነበር።**

የምንሸምታቸው ዕቃዎች ዝርዝር ጽፈን/ሊስት አድርገን ገበያ እንደምንሄድ ፣ ወያኔዎች የሥልጣን ግባቸውን ለማሳካትና ሥልጣናቸውን ለማራዘም አጥንተው በማኅደራቸው ያስቀመጥዋቸው የተለያዩ የሸብር፣ የማታለያና የውሸት ስልቶች አልዋቸው። "እሥረኞችን ፈትተን ማዕከላዊ ወደ ቤተመዘክረነት እንቀይረዋለን" ማለታቸው ፣ከእነዚህ በማኅደራቸው ካስቀመጥዋቸው ስልቶቻቸው አንዱ ነው ።እስቲ ጫካ ከነበሩበት ግዜ ጀምሮ የተጠቀሙባቸውን፣ የመገለባበጫና የውሸት ስልቶቻቸው የማስታውሰውን ያህል ልጠቁም ።

**የፖለቲክ ሥልጣን ለመጨበጥ የተጠቀሙባቸው የውሸት ስልቶች**

-የምንታገለው ትግራይ ከአማራ ቅኝ አገዛዝ አውጥተን ራሷ የቻለች አገር ለማድረግ ነው

-እኛ የአረብ ዘር ነን፣ትግራይ ነጻ ስትወጣ የአረብ ሊግ ማኅበር እንገባለን፣ በማለታቸው ሁሉንም የአረብ አገሮች በሚፈልጉትን ጉዳዮች ሁሉ ተባበሯቸው

-የምንከተለው የሶሻሊስት እርዮትና ኮማንድ ኢኮነሚ ነው ፣በተለይም የአልባኒያው ኤንቨርዎገ የሚከተለውን ሶሻሊዝም እንከተላለን

-ርዮታችን ወደ ሊበራል ዲሞክራሲ ፣ከኮማንድ ኢኮኖሚ ወደ የነጻ ገበያ/ማርኬት ኢኮኖሚ ቀይረናል አሉ ፣ስለሆነም በካፒታሊስት ዕራባውያን መንግሥታት ሁሉ ታቀፉ፣ለ26 ዓመታት ኢትዮጵያን ለ26 ዓመታት- እንዲገዙ፣እንዲሸጡ፣እንዲያፈርሱ፣እንዲያጠፉ ወዘተ.. ተባበሯቸው ፤ለምንያህል ተጨማሪ ዓመታት እንደሚያስቀጥሎቸው አይታወቅም

-ለሥልጣን ኮርቻ ሲያበቋቸው፣የመናገር፣የመጻፍ፣የመሰብሰብ፣የሰብአዊና የዲሞክራሲ..መብቶች እንፈቅዳልን የሚል ቃል ገብተውላቸው ነበረ፤ሥልጣናቸውን ካደላደሉ በኋላ ያንን ትተው ወደ ልማታዊ ዲሞክራሲ(developmental democracy) ቀየሩት ። ማለት ዲሞክራሲዊ ሥርዓት/አስተዳደር መምጣት ያለበት ከምጣኔ ሃብት እድገት ወይም ከልማት በኋላ መሆን አለበት በማለት ሙግት ገጠሙ ወዘተርፈ

**ሥልጣን ከጨበጡ በኋላ-ሥልጣናቸውን ለማራዘም የተጠቀሙባቸው የውሸትና የሽብር ስልቶች**

- የጫጉላ/ሃኒሙን ግዜያቸው አልቆ፣የኢሳያስ አፈወርቂ ሠራዊት እስከ መሃል ትግራይ ዘልቆ ሲወራቸው፣የትግራ ተወላጅ የሆኑትን የህወሃት ሠራዊት እንዳይነዳባቸውና ግንባር ላይ ላለማሰለፍ:-

  ?<1> ሥልጣን ሲጨብጡ ያባረሯቸውን የደርግ ወታደሮች እንዲደርሱላቸው ሲማጸኑ የሰባት<7> ዓመት ውዝፍ ወይም ያልተከፈለ ደሞዛቸውን እንደሚከፈላቸው ፣ ድሮ የነበራቸውን ማዕረግና ደሞዝ እንደሚሰጣቸው፣ ከጦርነቱም በኋላ የህወሃት ሠራዊት አካል ሁነው እንደሚቀጥሉ ተነግሯቸው ነበር። ነገር ግን ከጦርነቱ በኋላ የተባለውም ክፍያ ሳያገኙ መልሰው አባረርዋቸው

  <2> በጦርነቱ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ ከወያኔዎች ጎን ተሰልፎ ስለነበረ፣ ጦርነቱ በኢትዮጵያ ሕዝብ ድል አድራጊነት ስላለቀ ከጦርነቱ በኋላ በኢትዮጵያ ታርክ፣ ሰንደቃዓላማ ፣ ቋንቋ ፣የባህር በር ላይ ወዘተርፈ ለፈጸሟቸውን ደባ፣ንቀትና ማላገጥ ይቅርታ ይጠይቁ ይሆናል ፤ከኢትዮጵያ ሕዝብም ይታረቁ ይሆናል ተብሎ ተጠብቀው ነበር ። ነገር ግን ከያዙት መሠሪ አቋም ፈቀቅ አላሉም።
- የግዲያ ሽብር በመፍጠር ማለት ገሎ በማስደንገጥ - የ1997 ዓ.ም በየአደባባዩና በየደጃፉ የረሸኑትን፣ የቅርቡ የወልዲውን ፣የመርሳውን፣የቆበውን፣የሳርቃውን ወዘተርፈ የግዲያ ሽብሮች በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል

- የሕዝብ ጥያቄ መልስ መስጠት ስላልቻልን ነው፡- ከየቦታው ለሚሰሙ እሮሮዎች ተጠያቂው መንግሥት ነው ፤ስለሆነም አይዟችሁ ችግራችሁ እንፈታላችኋለን
- የአይስስና የአልሸባብ ሃይሎች ከድምጻችን ይስማ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ጋር ተሰልፎዋል፤አገራችሁ በእስላም አክራሪዮች ልትወረር ነው
- ችግሩ የተፈጠረው በክልል አስተዳዳሪዮች ድክመት እንጂ በማዕከላዊ መንግሥት ድክመት አይደለም ፤አጣርቶ ችግሩን የሚፈታ ሃይል እንልካለን
- ችግሩ የተፈጠረው ከኮንትሮባንድ ዕቃ ጋር በተያያዘ እንጂ ከድንበር ጋር በተገናኘ፤ ከአስተዳደር ጋር የተያያዘ አይደለም
- በወያኔዎች ላይ ሆ ብሎ የተነሱትን ኦሮሞ ወንድሞቻችንን ከሌሎች ኢትዮጵያውያንን ለማጋጨት፤ የፊንፍኔ ባለቤቶች ኦሮሞች ስለሆኑ የተለየ ጥቅም ይበጅላቸዋል
- ከፖለቲካ ድርጅቶች ጋር የማስመሴያ ድርድር መጅመር ፤ በአገር ቤት አንዳንድ ለስለስ ያሉትን የፖለቲካ ድርጅቶች ሰብስቦ ፤ ምን ዓይነት መንግሥት፣ምን ዓይነት ርዮት፣ምን ዓይነት የምርጫ ሥርዓት ቅብጥርሶ ያስፈልገናል እያለ የማይቋጭና የሥልጣን ማራዘሜ ውይይት መጀመር ወዘተርፈ።የወያኔዎች ትልቁ ችሎታ ውሸትና ጭፍን ድፍረቶች ናቸው።

One of the English idioms says "Lies/lice have got short legs"

(lice) ቅማል ሲሆን- በርግጥም ተፈጥሮ አጭር እግሮች ሰጥቷቸዋል

(lies) ውሸቶች- እውነትን ስላልያዙ ርቀው አይጓዙም፤ ቶሎ ይሸነፋሉ ለማለት ነው ።ታዲያ የህወሃት/ወያኔዎች ውሸቶች ለምን የተለየ ሆኑ? እንዴት ለ26 ዓመታት አዘለቃቸው? በጠመንጃ አፈሙዝ ስለታጀቡ ይሆን?